# ጊዜ ለኩሉ!

## የእግዚአብሔር ወፍጮ በፍጥነት  ባይፈጭም ሲፈጭ ግን በደንብ አልሞ እና አድቆ ነው!

በዚያ በደጉ ዘመን እንደምታስታውሱት የሠማያዊ ፓርቲ እና አንዳንድ የአማራ ክልል፣ የዞን እና የክልል ብአዴን ጉጅለዎች የፖለቲካ አጀንዳቸው ከአንድ ድርሳናት ይቀዳ ነበር፡፡ በቅማንት የማንነት እና የራስ አስተዳደር ጥያቄ  ዙሪያ ላይ ብአዴንም ሆነ ሰማያዊ ፓርቲ ምንም አይነት ልዩነት የላቸውም፡፡ ትምህክት የተጠናወታቸው የብአዴን አባላትም ሆኑ አብዛኛው የሰማያዊ ፓርቲ አባላት በምንም መንገድ በህዝቦች እኩልነት አያምኑም፡፡ እንዲያውም ሰማያዊ ፓርቲ የስሙ መነሻ  (ሰማያዊ የሚለው ቃል) ሥልጣን የህዝብ ሳይሆን በሰዩም- ፈጣሪ  (Devine power) የሚቸር ነው ብሎ የሚያስብ እና የወደቀውን የኃይለሥላሴ የፊውዳል ሥርዓት (ሞኣ አንበሳ ዘእምነ ነገድ ይሁዳ) በዋናነት የሚያቀነቅን ድርጅት ነው፡፡

የዚህ ፖለቲካ ድርጅት ሥርወ- አመጣጡ (genesis)  ከአንድ በዘር ከተደራጀ የፖለቲካ ድርጅት ራሱን አባዝቶ እና አካፍሎ ከዚህ የደረሰ ድርጅት ነው፡፡ ይህ ድርጅት በአደባባይ የሚያቀነቅነው በዘር ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝም ለኢትዮጵያ አይበጅም፣ በሂደትም ኢትዮጵያን የመበታተን አደጋ አለው ይበል እንጅ ውስጡ ሲፈተሽ ግን የመጨረሻ  ግቡ  ያ መስቀል በእግሩ የያዘውን የይሁዳ አንበሳ ብለው የሚጠሩት አውሬ ያለበትን  ባንዴራ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ዳግም ማውለብለብ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት አንቀጽ 3 ስለኢትዮጵያ ባንዴራ እንዲህ በማለት ያትታል፡፡ «የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሀል ቢጫ ከታች ቀይ ሆኖ በመሀሉ ብሔራዊ አርማ ይኖረዋል» ካለ በኋላ የአርማውን  ትርጉም እና አላማ እንዲህ በማለት ያስቀምጣል፡፡«ከሰንደቅ ዓላማው ላይ የሚቀመጠው ብሔራዊ ዓርማ የኢትዮጵያን ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣  ሕዝቦች እና ሀይማኖቶች በእኩልነት እና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንፀባርቅ ይሆናል» ይላል፡፡ ሁላችሁም በደንብ አነበባችሁት? ይህ ዓርማ ምን ስህተት አለበት? ለእነዚህ ቡድኖች የዚህ ዓርማ ስህተት ልንገራችሁ የአትዮጵያን ህዝቦች አንዱ ታላቅ ሌላኛው ትንሽ ፣ አንዱ አምነት የበላይ ሌላኛው የበታች አለማለቱ ነው፡፡

ይሁንእንጅ ሰሞኑን በጎንደር፣ በባህርዳር እና በአማራ ክልል አንዳንድ ከተሞች በተደረገው ህገ-ወጥ ሰለፍ ላይ የተከወነው እና በግልፅ የታየው ይህን የአንድነት አርማ በግልፅ የሚሽር እና ህገ-መንግሥቱን በግልፅ የጣሰ ድርጊት ነበር፡፡ እነዚህ ህገ-ወጥ ሰልፈኞች የኢትዮጵያን ህዝቦች ህብር እና የሀይማኖትን እኩልነት የሚያሚያመለክት አርማ  ያለውን የኢትዮጵያ ባንዴራ አውርደው  በእሳት አጋይተው በምትኩ እነሱ የእኛ የሚሉትን ባንዴራ ህገ-ወጥ ሰልፍ በተካሄደባቸው ከተሞች አውለብልበዋል፡፡ ይህ አድራጎታቸው ተጨማሪ ትርጉም የሚያስፈልገው አይመስለኝም፤ እጅግ ግልፅ ነው፡፡  ሁሉም ህዝቦች  እኩል የሆኑባት እና ሁሉም ሀይማኖቶች በቡድን እና በተናጠል ያለመሸማቀቅ እና በነፃ ፍላጎት የሚመለከባት ኢትዮጵያ  ጠፍታ እነዚህ ቡድኖች እና መሰሎቻቸው የሚመኟት የብሔረሰቦ እስር ቤት የሆነችውን አገር መመለስ ነው፡፡ ይሳካ ይሆን? አብረን እናያለና!

ለእነዚህ ቡድኖች ከእነሱ በስተቀር ሁሉም ህዝብ መጤ ነው፤ ሌላው እምነት እና ሀይማኖት የአረማዊ (pagan) እምነት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ መጤ የሚባሉ  ህዝቦችም አንድም የራሳቸውን ማንነት አውልቀው ጥለው ከእነሱ ጋር መዳበል አለባቸው ይህ ካልሆነ ደግሞ ከኢትዮጵያ ምድር- ገፅ  መጥፋት ይጠበቅባቸዋል ይህ ካልሆነ ደግሞ ሌላው አማራጫቸውጭ ጭቆናን አሜን ብለው  ሳያቅማሙ መቀበል ይኖርባቸዋል፡፡ ሰማያዊ ፓረቲን እና የተወሰኑ ፅንፈኛ የብአዴን አመራሮች ለባለፉት ዓመታት አንድ ያደረጋቸው ይህ የጋራ አመለካከታቸው ነበር፡፡ የክልል የዞን እና የወረዳ ብአዴን አመራሮች ከላይ የብአዴንን ካባ ወዘፍ አድርገው  በውስጣቸው ግን ደማቅ ሰማያዊ ቀለም ያለው አርማ ያለበትን ርእዮት አለም ለእነርሱም ለተከታዮቻቸውም ያሰርፃሉ፡፡ በአማራ ክልል ከብአዴን ድርጅት ይልቅ ሰማያዊ ፓርቲ  የላቀ ክብር አለው፡፡

ለተወሰኑ የብአዴን አመራሮች የብሔረሰቦች እኩልነት ዋጋ እንደሌለው ሁሉ ለሰማያዊ ፓርቲም ያው ዋጋ የለውም፡፡በእነዚህ ምክንትያቶች እነዚህ ቡድኖች እንደመፍትሔ የሚያቀነቅኑት  የፌደራል ሥርዓቱን በሀይ በመናድ ኢትዮጵያን ወደ ብሔረሰቦች እስርቤት መመለስ አለያም በእርስ በእርስ ጦርነት መለብለብ፡፡

ይህን እያልኩ ያለሁት ለአንዳንድ ፅንፈኛ የብአዴን አባላትም ሆነ ለሰማያዊ ፓርቲ ካለኝ ግላዊ ጥላቻ ሳይሆን ከተግባራቸው በመነሳት ነው፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ የቅማንት ህዝብ እንደሌሎች ህዝቦች ማንነቴ ታውቆ፣ ባህል እና ቋንቋየ ተከብሮ በእኩልነት ላይ በተመሰረተ አንድነት በአጎራባች ከሚገኙ የአማራ ህዝቦችም ሆነ ከሌሎች ህዝቦች ጋር በአንደነት ልኑር ብሎ ህገ-መንግሥታዊ ጥያቄ ሲያቀርብ በመጀመሪያ ተቃውሞ የገጠመው ከህዝብ ሳይሆን በአመራሩ ቁንጮ ባሉ የብአዴን አባላት ነበር፡፡ ለኢህአዴግ የቅማንት ጥያቄ አለመመለስ ጉዳዩን የቅማንት ጥያቄ አድርጎ ተመልክቶት ከሆነ ትልቅ የዋህነት ነው፡፡ ህገ-መንግሥቱ ለህዝቦች ያጎናፀፈው ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በተለያዩ ተልከሻ  ምክንያቶች ለቅማንት ህዝብ ሲከለከል ትርጉሙ ሰፊና ጥልቅ ነበር፡፡ «መልዕክቱም በክልሌ እና እኔ በማስተዳድርበት ግዛት የህገ-መንግሥቱ አንቀፆች ቦታ የላቸውም፤ ተሽረዋል እንደማለት ነበር፡፡ ኢህአዴግ ሆየ ይህን ጉዳይ

የቅማንት ብቻ አድርጎ ተመለከተው እና በዚህ መሰላል ወደላይ መውጣት የጀመሩ ቡድኖች በሀይል ህገ-መንግሥቱን የሚንድ ቡድን በገሀድ ማደራጀት እና መምራት ተያያዙት፡፡ ውጤቱንም አብረን እያየነው ነው፡፡ ለቅማነት ጥያቄ አለመመለስ ብአዴን ብቻ ሳይሆን ሁሉም የግንባሩ አባላት እና ሌሎች አጋር ድርጅተቶች ሀላፊነት አለባቸው፡፡

በ2006 ዓ.ም የቅማንት ህዝብ ሰላማዊ ሰለፍ በጎንደር ከተማ ለማድረግ ለከተማ አስተዳደሩ (ለከንቲቫ ጽ/ቤት) ጠይቆ ፈቃዱ ከተፈቀደ እና ሙሉ የሰልፉ  ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ  የዞን አስተዳደሩ እና የከቲቫ  ጽ/ቤት ለሰማያዊ ፓርቲ ያላቸወን አጋርነት ለማሳየት የሚከተለውን አደረጉ፡፡ የቅማንት ህዝብ ሰለፍ በሚወጣበት ቀን ሰማያዊ ፓርቲ ሰለፍ እንዲጠራ በመምክር በተመሳሳይ ቀን በተመሳሳይ ቦታ እና ሰኣት ሰላማዊ ሰልፍ እንዲወጣ ተፈቀደለት፡፡ ይህ ወቅት በተለይለቅማንት ኮሚቴ አመራሮች  በአጠቃላይ ደግሞ ለቅማንት ህዝብ ሰላማዊ ትግል እጅግ ፈታኝ ጊዜ ነበር፡፡ ግማሹ የቅማንት ኮሚቴ  ህዝብ ከጠራን በኋላ የሰልፉን ቀን ከምንቀይረው ጎን ለጎን ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር እናድርግ ሲል ሌላው ደግሞ በፍፁም መደረግ የለበትም በሚል ፈታኝ የሆነ አተካራ ገብቶ ነበር፡፡ በመጨረሻም መደረግ የለበትም ከሚለው ድምዳሜ ላይ ተደርሶ ቅዳሜ ሰልፉ ሊደረግ አርብ ማታ ለህዝብ ሰልፉ እንደተሰረዘ ተነገረ፡፡

ይሁን እንጅ የዚህ ድርጊት ደብቅ የብአዴን አመራሮች ዓላማ ‹‹በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ››  ለማለም አስበው ነበር፤ አልተሳካም እንጅ፡
፡

አንደኛዋ የምትሞተው ወፍ የማንነት ጥያቄ የጠየቀችው የቅማንት ትግል ነበረች፡፡ ወፏን  በሰበብ  ለመግደል ብአዴኖች  በግልጽ የሚደግፉትን ሰማያያዊ ፓርቲ ( ነገር ግን ለቅማንት ሲባል እንደተቃዋሚ የሚታየው ድርጅት) ጋር የቅማንት ህዝብ ሰለፍ በመውጣቱ የቅማንት ኮሚቴ ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር አብሮ እየሰራ ነው ብሎ ሙሉ በሙሉ እንቅስቃሴውን ማስቆም እና አመራሮችን ወደ እስር ቤት ማጋዝ እንዲሁም ድርጊቱን በሀሰት ለእነሱ የተዛባ የፖለቲካ   መጠቀሚያ ማድረግ ነበር፡፡

ሌላኛዋ ወፍ የምትሞት ሳትሆን በድንጋዩ አማካኝነት ወደላይ እንድትበር የምትደረግ ነበረች፡፡ እሷም ሰመያዊ ፓርቲ ናት፡፡ የቅማንት ህዝብ በዚህ ቀን ሰልፉን ስለሚያጥለቀልቀው ይህ ህዝብ ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር አብሮ ከወጣ ሰማያዊ ፓርቲ የሌለውን የህዝብ ድጋፍ እንዳገኘ ተደርጎ በአማራ ቴሌቪዥን አብይ ዜና መስራት ነበር፡፡ በዚህ የሰማያዊ ፓርቲ ሰልፍ ላይ የሰልፍ ወረቀት ሲበትኑ የነበሩት ግን የመንግሥት አመራሮች ነበሩ፡፡

ግን ያ ሁሉ ሳይሆን ቀረ እና የቅማነት የሰላማዊ ሰለፍ ቀን ተቀየረ እና በዚያ ቀን ሰማያዊ ፓርቲ ከ100 አስከ 150 የሚሆኑ ህፃናትን አሰልፎ ትንሽ መፎክር ፒያሳ ላይ አሰምቶ ተበነ፡፡ በሌላኛው ቀን የቅማንት ህዝብ ትኢንንተ-ህዝብ ጎንደርን አጠልቀለቀው፡፡ይህን ህዝብ ነበር ለሰማያዊ ፓርቲ ድጋፍ ሊሰጥ ታስቦ የነበረው፡፡

ዛሬ ግን ነገሩ ወዲህ ነው፡፡ የእነዚህ ጠባብ የተወሰኑ የብአዴን አመራሮች ህገ-መንግሥቱን የማፍረስ ሴራ በግልፅ በጎንደር እና በባህር ዳር ነውጥ ይፋ ሲወጣ እነዚህ ቡድኖች የሚያመካኙበት የመስዋት ፍየል (scapegoat) አስፈለጋቸው፡፡ የያኔው ወረቀት ተብትኖለት ቅማንት በጠራው ሰላማዊ ሰለፍ ላይ እንደታቦት ተደርቦ  እንዲወጣ የተከበከበው ሰማያዊ ፓርቲ በባህርዳር የተካሄደውን እና ለንብረት እና ለብዙ ህይዎተ- እልፈት ምክንያት የሆነውን ሰልፍ ኃላፊነቱን እንዲወስድ መግለጫ ወጥቶበታል፡፡ ምክንያቱም  ይህን ሰለፍ ሰማያዊ ፓርቲ ካልወሰደው ባለቤት አልባ ሊሆን ነዋ ጉዳዩ፡፡አሁን ሰማያዊ ፓርቲ ይህን ሰለፍ አንደተመሳሳይ የካርታ ጨዋታ ‹‹ሞንቴ›› ብሎ የሚጥለው ሳይሆን በሞንቴው ተጫውቶ ኪሳራውን መቀበል የግድ ነው፡፡ ጀግኖች አሁን ሀሪፍ ጆከር ስበዋል፡፡ የጎንደሩ ሰለፍ ግን የሚወስድላቸው አካል (የአገር ውስጥ ስሬት የፖለቲካ ድርጅት ማለቴ ነው) አስካሁን ያገኙ አይመስለኝም፡፡

የእግዚአብሔርን ወፍጮ ታምር አያችሁልኝ! ቀስ አድርጎ  ሁሉንም ማድቀቅ ጀምሯል፡፡

የሚገርመው ሰማያዊ ፓርቲ ተሳስቶ ስለቅማንት ህዝብ መጨፍጨፍ መግለጫ አውጥቶ ሰምታችሁት ታውቃላችሁ? ወይም ደግሞ ኢንጂኒይር ያረጋል ጌትነት በቪኦኤ ወይም በሌላ መድረክ ሲናገሩ ቅማንት ስለደረሰበት ግፍ እና በደል አፋቸው አምልጧቸው እንኳ በቅማንት ላይ የተፈፀመውን ግፍ አንስተው ያውቃሉ? ታዲያ ይህ ፓርቲ የዚህ ፓርቲ መሪ  ስለየትኛው አንድነት ነው የሚሰብከን?

ጊዜ ለኩሉ ያለው ጠቢብ ማን ነበር?